የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

# ፌደራል ነጋሪት ጋዜጣ

# FEDERAL NEGARIT GAZETTE

**OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA**

ሃያ ሦስተኛ ዓመት ቁጥር
አዲስ አበባ ግንቦት ፳፰ ቀን ፪ሺ፱ ዓ.ም

በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ

23rd Year No.
ADDIS ABABA, 5th June, 2017

**ማውጫ**

**አዋጅ ቁጥር ፩ሺ፶፩/፪ሺ፱ ዓ.ም**

የቡና ግብይትና ጥራት ቁጥጥር አዋጅ ቁጥር ..................................፱ሺ፮፻፶፯

**CONTENT**

Proclamation No.1051 /2017

Coffee Marketing and Quality Control Proclamation Proclamation……………………………………………page 9657

አዋጅ ቁጥር ፩ሺ፶፩/፪ሺ፱

**የቡና ግብይት እና ጥራት ቁጥጥር አዋጅ**

በዓለም አቀፍ ገበያ ተወዳዳሪ የሆነ በጥሬወና እሴት የተጨምረበት የቡና ምርት በጥራትና በከፍተኛ መጠን፣ ቀጣይነት ባለውና የምርት ዱካውን በጠበቀ ሁኔታ ለማቅረብ የሚያስችል የቡና ግብይትና ጥራት ቁጥጥር ሥርዓት ማዘርጋት በማስፈለጉ፣

የቡና ግብይትን ዘመናዊነት፣ ህጋዊነትና ፍትሃዊነት በማሻሻል የቡና አምራቾች፣ የግብይት ተዋንያንና የሀገሪቱን ተጠቃሚነት በላቀ ደረጃ ማሳደግ የሚያስችል የተለያየ አማራጭ ያለው የግብይት ሥርዓት ማዘርጋት አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ፣

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ህገ መንግሥት አንቀፅ ፶፭ (፩) መሠረት የሚከተለው ታውጇል፡፡

‹

**ክፍል አንድ**

**ጠቅላላ ድንጋጌዎች**

**፩. አጭር ርዕስ**

**PROCLAMATION NO. 1051 /2017**

**A PROCLAMATION TO PROVIDE FOR COFFEE MARKETING AND QUALITY CONTROL**

**WHEREAS** it has become necessary to establish a sustainable and traceable coffee marketing and quality control system which enables supply of quality, voluminous and competitive unfrosted and value added coffee to the global market;

**WHEREAS,** it has been found necessary to establish modern, legal and fair alternative coffee transaction system, in order to boost the benefits of coffee producers, transaction actors and the country;

**NOW, THEREFORE,** in accordance with Article 55 (1) of the Constitution of the Federal Democratic Republic of Ethiopia it is hereby proclaimed as follows:

ይህ አዋጅ "የቡና ግብይትና ጥራት ቁጥጥር አዋጅ ቁጥር ፩ሺ፶፩/፪ሺ፱" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

## ፪. ትርጓሜ

የቃሉ አገባብ ሌላ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር በዚህ አዋጅ ውስጥ፡ −

፩/ "ቡና" ማለት በማንኛውም ዓይነትና የዝግጅት ደረጃ የሚገኝ የቡና ተክል ፍሬ ወይም የፍሬው ክፍል ነው፤

፪/ "ቀይ እሸት ቡና" ማለት በተፈጥሮ የብስለት ደረጃ ላይ ደርሶ የተለቀመ እና ያልተፈለፈለ የቡና ፍሬ ነው፤

፫/ "ጀንፈል ቡና" ማለት ቀይ እሸት ቡና በወቅቱ ተለቅሞ፤ በማድረቂያ አልጋ ወይም ከሲሚንቶ በተሰራ አወድማ ላይ ወይም በተፈቀደ ሌላ ማድረቂያ ላይ የደረቀና ያልተቀሸረ የቡና ፍሬ ነው፤

፬/ "የታጠበ ቡና ከነገለፈቱ" ማለት በባለሥልጣኑ ወይም አግባብ ባለው የክልል አካል በተፈቀደ የቴክኒክ አሰራር ቀይ እሸት ቡና በመፈልፈል፣ በማብላት ወይም ሳይቦካ በማዘፍዘፍ፣ በማጠብና በማድረቅ ተዘጋጅቶ ከነ−ሸማዙ ያለ ቡና ነው፤

፭/ "የታጠበ ቡና" ማለት በባለሥልጣኑ ወይም አግባብ ባለው የክልል አካል በተፈቀደ የቴክኒክ አሰራር ተዘጋጅቶ ገለፈቱና ስስ ልባሱ የወጣለት ቡና ነው፤

፮/ "በከፊል የታጠበ ቡና" ማለት በባለሥልጣኑ ወይም አግባብ ባለው የክልል አካል በተፈቀደ የቴክኒክ አሠራር ቀይ እሸት ቡና በመፈልፈል ከነልጋጉ በማድረቅ የተዘጋጀ ቡና ነው፤

፯/ "ተፈጥሯዊ ወይም ያልታጠበ ቡና" ማለት በባለስልጣኑ ወይም አግባብ ባለው የክልል አካል በተፈቀደ የቴክኒክ አሠራር ጀንፈል ቡናን በመቀሸርና በማበጠር የተዘጋጀ ቡና ነው፤

፰/ "ልዩ ቡና" ማለት በአመራረቱ፣ በአዘገጃጀቱ እና በጥራቱ የተለየ ስለመሆኑ በማስፈርት አግባብ ባለው አካል ተማክሮለት ከሌሎች ቡናዎች በተሻለ ዋጋ የሚሸጥ ቡና ነው፤

፱/ "አቅርቦት ቡና" ማለት በአምራች አካባቢ ባሉ ኢንዱስትሪዎች ተዘጋጅቶ ለኢትዮጵያ ምርት ገበያ ወይም

## SECTION ONE
## GENERAL PROVISIONS

### 1. Short Title

This Proclamation may be cited as the "Coffee Marketing and Quality Control Proclamation No.1051/2017".

### 2. Definition

Unless the context requires otherwise, in this Proclamation:

1/ "coffee" means the fruit of a coffee tree or parts of such fruits in whatever form and processing;

2/ "red cherry coffee" means the red fruit of a coffee tree picked after it is naturally ripened but not pulped;

3/ "coffee with pulp" means a red cherry coffee picked timely and dried in bed or a place made by cement or in other technically allowed means but not hulled;

4/ "washed coffee with parchment" means red cherry coffee which has been pulped, fermented or not washed and dried with its husk through allowed technical procedures set by the Authority or relevant regional states;

5/ "washed coffee" means red cherry coffee which has been removed its sticky mucilage and parchment through allowed technical procedures set by the Authority or relevant regional states;

6/ "semi-washed coffee" means dried and pulped red cherry coffee with its sticky mucilage through allowed technical procedures set by the Authority or relevant regional states;

ለኤክስፖርት ማዘጋጃ ኢንዱስትሪዎች በቀጥታ የሚቀርብ ቡና ነው፤

፲/ "የወጪ ገበያ ቡና" ማለት የአገሪቱን የወጪ ገበያ ቡና የጥራት ደረጃ ማስፈርትና የገዢውን ፍላጎት በጠበቀ ሜልኩ በጥሬው፣ ተቆልቶ፣ ተፈጭቶ ወይም በሌላ ሜልኩ እሴት ተጨምሮበት የተዘጋጀ ቡና ነው፤

፲፩/ "ተረፈ ምርት ቡና" ማለት ቡናን በማዘጋጀት ሂደት የሚወጡ ያልፈረጠሙ ወይም ልቃሚ ወይም ሰባራ እና ገለባ ያሉበትን ቡና ያጠቃልላል፤

፲፪/ "የሀገር ወስጥ ፍጆታ ቡና" ማለት ቡና ሲዘጋጅ የሚወጣ ተረፈ ምርት ቡና ወይም የጥሬና ጣዕም ምርመራ ወጤቱ ከ ፲፭ በመቶ ያልበለጠ ንጹህ ቡና ሆኖ ለወጪ ገበያ የማይላክ ቡና ነው፤

፲፫/ "መርቡሽ ቡና" ማለት በመቀጫ ወይም በድንጋይ ወፍጮ ወይም በሌላ ኋላ ቀር በሆነ መንገድ የተዘጋጀና የኤክስፖርት ደረጃ የማያሟላ ቡና ነው፤

፲፬/ "ቡና አቅራቢ" ማለት አግባብ ካለው የክልል አካል የብቃት ማረጋገጫ የቡና ንግድ ፈቃድ የተሰጠው ቀይ እሸት ወይም ጀንፈል ቡና በተፈቀደ የማበያያ ስፍራ ወይም ህጋዊ የልማትና ግብይት ትስስር ከፈጠሩ አርሶ አደሮች በመግዛት ወይም ከራሱ ማሳ ወይም ህብረት ሥራ ማህበር ከሆነ ከአባላት በማሰብሰብና በማዘጋጀት ለኢትዮጵያ ምርት ገበያ ወይም በህግ አግባብ በቀጥታ የግብይት ትስስር ለላኪ ወይም ለውጭ ገበያ የሚያቀርብ ሰው ነው፤

፲፭/ "ቡና አልሚ እና ላኪ" ማለት አግባብ ካለው መንግሥታዊ አካል የብቃት ማረጋገጫ የቡና ላኪነት ንግድ ፍቃድ የተሰጠው ሆኖ በማሳው ያመረተውን ወይም በህግ አግባብ የልማትና ግብይት ትስስር ከፈጠሩ አርሶ አደሮች ወይም ከህብረት ሥራ ማህበር አባላት የተሰበሰበን ቡና ለወጪ ገበያ በሚመጥን ደረጃ አዘጋጅቶ የሚልክ ሰው ነው፤

፲፮/ "ቡና ላኪ" ማለት አግባብ ካለው መንግስታዊ አካል የብቃት ማረጋገጫ የቡና ላኪ ንግድ ፍቃድ የተሰጠወና በህግ አግባብ በተፈጠረ የግብይት ትስስር ወይም ከኢትዮጵያ ምርት ገበያ የገዛውን ቡና ለወጪ ገበያ በሚመጥን ደረጃ አዘጋጅቶ የሚልክ ሰው ነው፤

፲፯/ "የመጀመሪያ ደረጃ የቡና ግብይት ማዕከል" ማለት በቡና

7/ "natural or sun dried coffe " means coffee with pulp hulled, cleaned and sorted through allowed technical procedures set by the Authority or relevant regional states;

8/ "special coffee" means coffee certified in its special production, process and quality by standards of relevant organ and sell in a better price than the other coffees;

9/ "supply coffee" means coffee processed by industries located in the production area for delivery directly to the Ethiopia Commodity Exchange or export processing industries;

10/ "export coffee" means raw, roasted, roasted and grinded or processed in other value added form in compliance with the country's export quality standard and buyer needs for export;

11/ "coffee by product" means coffee mixed with light, broken, under developed coffee and coffee husk;

12/ "domestic consumption coffee" means coffee not exportable, consisting a total of 15% pure coffee and coffee by product.

13/ "traditionally processed coffee" means coffee processed using outdated methods of wood or stone grinder, which does not fit export level;

14/ "coffee supplier" means a person who,is certified and licensed to trade coffee by the appropriate regional states, upon meeting the required criteria, collects prepares and processes coffee with pulp or red cherry coffee from auction

አምራች አካባቢዎች አግባብ ባለው የክልል አካል የተፈቀደ ቀይ የእሸት ወይም የጀንፈል ቡና መገበያያ ሥፍራ ነው፤

፲፰/ "ሌሎች የቡና ግብይት አማራጮች" ማለት የቡና ጥራት በማሻሻልና የተሻለ ዋጋ በማስገኘት አምራቾችንና የግብይት ተዋንያንን ተጠቃሚ የሚያደርግ መሆኑ በባለሥልጣኑ ተረጋግጦ የሚፈቀድ ከምርት ገበያው ወጪ የሚከሄድ የቡና ግብይት መድረክ ነው፤

፲፱/ "የቡና ግብይት" ማለት ህጋዊ የግብይት ሥርዓትን በመከተል በመጀመሪያ ደረጃ ግብይት ማዕከላት፣ በምርት ገበያው፣ በውጪ ገበያ ወይም በሌሎች የግብይት አማራጮች በአምራቾች፣ በአቅራቢዎች፣ ላኪዎች፣ እሴት በሚጨምሩ ኢንዱስትሪዎችና የውጭ ቡና ገዢ ኩባንያዎች እንዲሁም በጅምላ ነጋዴና ቸርቻሪ መካከል የሚከናወን የቡና ግዢና ሽያጭ ሂደት ነው፤

፳/ "የቡና ጥራት ቁጥጥር" ማለት ቡና የተፈጥሮ ባህሪውንና ጣዕሙን እንደጠበቀ ለተጠቃሚው ለማቅረብ ከምርት ማሰብሰብ ጀምሮ በግብይት፣ በምርት ዝግጅት፣ በአከማቻቸት፣ በመቁላት ወይም በመቁላትና በመፍጨት፣ በማሸግና በማጓጓዝ ሂደት በተፈቀደ የአሠራር ሥርዓት እና የጥራት ደረጃ ማስፈርት መሠረት ስለመከናወኑ በየደረጃው የሚፈጸም የቁጥጥር ተግባር ነው፤

፳፩/ ''ቡና ማዘጋጀት'' ማለት በሀገሪቱ በተፈቀደ የጥራትና ደረጃ የቴክኒክ አሰራር ማሰረት በመጀመሪያ ደረጃና በኤክስፖርት ማዘጋጃ ኢንዱስትሪዎች የታጠበ ቡና፣ በከፊል የታጠበ ቡና ወይም ተፈጥሯዊ ወይም ያልታጠበ ቡና በጥሬው የማዘጋጀት ሂደትን ያጠቃልላል፤

፳፪/ ''እሴት የሚጨምሩ ኢንዱስትሪዎች'' ማለት ቡናን ቆልተው ወይም ቆልቶወና ፈጭተው ወይም በተለያዩ ሜልኩ አቀናብረው ለሃገር ውስጥ ወይም ለውጭ ገበያ የሚያቀርቡ ኢንዱስትሪዎች ናቸው፤

፳፫/ ''እሴት የተጨመረበት ቡና ማዘጋጀት'' ማለት በተፈቀደ የቴክኒክ አሰራር መሠረት ጥሬ ቡናን ቆልቶ፣ ቆልቶና ፈጭቶ ወይም ወደ ተለያየ ዓይነት ምርቶች የማቅነባበር ሂደት ነው፤

centers or producers integrated with legal and developmental auctions or from his own farm or from members of cooperatives for delivery to the Ethiopia Commodity Exchange or directly to exporters with lawful transaction line or export market;

15/ "coffee producer and exporter" means a person who has obtained certificate of competence and coffee export business license from appropriate government organ either by collecting from his own farm or out growers in accordance with law, and coffee cooperatives collected from its members and exports coffee in compliance with the export quality and standards;

16/ "coffee exporter" means a person who, upon being licensed to trade coffee by the appropriate government organ, and upon purchasing coffee from the transaction integrated lawful line or the Ethiopian Commodity Exchange, processed and exports coffee in compliance with the export quality and standards;

17/ "first level coffee transaction center" means a center of transaction for red cherry coffee or coffee with pulp transaction upon being authorized by appropriate government organ of the coffee producing areas;

18/ "other alternative coffee transaction" means a special coffee transaction option which is different from Ethiopian Commodity Exchange transaction, verified and authorized by the Authority in accordance with law to enable improvement of coffee quality and helps to obtain better price and benefits to producers and transaction actors;

19/ "coffee transaction" means the lawful buying and selling of coffee in first level coffee transaction centers, exchange market, foreign market or in other alternative transactions

፳፬/ ‘‘የቡና አምራቾች’’ ማለት አነስተኛ ይዞታ ያላቸው ቡና አምራች አርሶ አደሮች፣ የቡና አምራች ህብረት ሥራ ማህበራት እና አልሚ ባለሀብቶች ናቸው፤

፳፭/ ‘‘የቡና ጥራት ምርመራና ደረጃ ምደባ ማዕከል’’ ማለት የብቃት ማረጋገጫ የሥራ ፈቃድ በባለሥልጣኑ ተሰጥቷቸው የአቅርቦት ቡና ጥራትና ጣዕም በመመርመር ደረጃ ለመመደብ በቡና አምራች አካባቢዎች አገልግሎት እንዲሰጥ የተቋቋመ መንግስታዊ ወይም የግል ድርጅት ነው፤

፳፮/ "የቡና ጥራት ምርመራና ሰርተፊኬሽን ማዕከል" ማለት ለውጭ ሀገር ገበያ በጥሬው፣ ተቆልቶ ወይም ተቆልቶና ተፈጭቶ የሚቀርብ ቡና የጥራት ደረጃ በማረጋገጥ የምስክር ወረቀትና የምርት ሀገር ሰርተፍኬት የሚሰጥ ማዕከል ነው፤

፳፯/ "የቡና ግብይት ማዕከላት" የመጀመሪያ ደረጃ ቡና ግብይት ማዕከላት እና የኢትዮጵያ ምርት ገበያን ያጠቃልላል፤

፳፰/ "የቡና ንግድ" ማለት አግባብ ካለው የመንግስት አካል የቡና ብቃት ማረጋገጫ እና ንግድ ፈቃድ አግኝቶ ቡና ከአምራቾች በመግዛት ወይም በማምረት አዘጋጅቶ ለኢትዮጵያ ምርት ገበያ ማቅረብን፣ በጥሬው ወይም ቆልቶ ወይም ቆልቶና ፈጭቶ ወደ ውጭ ሀገር መላክን፣ ከምርት ገበያው ገዝቶ ማከፋፈልን፣ መቸርቸርን የሚያጠቃልል ነው፤

፳፱/ "የሀገር ውስጥ ፍጆታ ቡና ጅምላ ነጋዴ" ማለት አግባብ ካለው መንግስታዊ አካል የሀገር ውስጥ ፍጆታ ቡና የጅምላ ንግድ የብቃት ማረጋገጫ ፈቃድ አወጥቶ ከኢትዮጵያ ምርት ገበያ ለወጪ ገበያ የሚይወል ቡናን በመግዛት በተፈቀደለት አካባቢ ለሚገኙ የቡና ቸርቻሪዎች ብቻ የሚያከፋፍል ሰው ነው፤

፴/ "ቡና ቸርቻሪ ነጋዴ" ማለት አግባብ ካለው መንግስታዊ አካል የሀገር ውስጥ ፍጆታ ቡና የችርቻሮ ንግድ ብቃት ማረጋገጫ ፈቃድ የተሰጠው ከሀገር ውስጥ ፍጆታ ቡና ጅምላ ነጋዴ ብቻ በመግዛት ለተጠቃሚዎች የሚሸጥ ሰው ነው፤

፴፩/"የወጪ ቡና ቆዪ" ማለት አግባብ ካለው የመንግሥት አካል የወጪ ቡና ቆዪነት የብቃት ማረጋገጫ የንግድ ፈቃድ የተሰጠው ከኢትዮጵያ ምርት ገበያ፣ ከራሱ ማሳ አምርቶ

options between producers, suppliers, exporters, value added industries and foreign coffee importer companies as well as wholesaler and retailers;

20/ “coffee quality control” means inspection and control of the picking, transaction, processing, storage, roasting or roasting and grinding, packaging and transportation of coffee, in accordance with acceptable norms and quality standards, to ensure delivery of coffee to consumers in its natural state;

21/ “coffee processing” means a process which includes washing coffee, semi washed coffee and natural and sun dried processing of coffee in first level and export processing industries in accordance with the country’s quality and grade requirements and the buyers’ needs as per the authorized technical procedures;

22/ “value added industries “means industries that roast or roast and grind or process in other forms of coffee product for domestic or export market;

23/ “value added coffee processing” means the process of roasting,roasting and grinding or changing in to various forms per the authorized technical procedures;

24/ “coffee producer” means small-scale coffee farmers, coffee farmers’ co-operatives and commercial growers;

25/ “coffee quality inspection and grading center” means a

ወይም በሌሎች የግብይት አማራጮች ቡና በመግዛት ቀልቶ ወይም ቀልቶና ፈጭቶ ለወጪ ገበያ በሚመጥን ደረጃ አዘጋጅቶ የሚልክ ሰው ነው፤

፴፪/ "የሀገር ውስጥ ቡና ቀይ" ማለት አግባብ ካለው የክልል አካል የሀገር ውስጥ ቡና ቀይነት የብቃት ማረጋገጫ ንግድ ፈቃድ የተሰጠው ለሀገር ውስጥ ገበያ ሊውል የሚችል ቡና ከኢትዮጵያ ምርት ገበያ ገዝቶ ቀልቶ ወይም ቀልቶና ፈጭቶ ለሀገር ውስጥ ገበያ የሚያቀርብ ሰው ነው፤

፴፫/ "የልማትና ግብይት ትስስር" ማለት የቡና አልሚነት ፈቃድ በተሰጠው ባለሀብት እና ኩታገጠም ወይም በዙሪያው የሚገኙ የቡና አምራች አርሶ አደሮች መካከል የጋራ ፍላጎትና ተጠቃሚነት ላይ የተመሠረተ ሆኖ በኤክስቴንሽን አገልግሎትና የቴክኖሎጂ አቅርቦት ትስስር በማድረግ ምርታማነትና የምርት ጥራት ለማሻሻል እና ለማበያየት የሚፈጠር ህጋዊ ግንኙነት ነው፤

፴፬/ "የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት" ማለት የቡና ግብይትን ለማከናወን፣ ለማዘጋጀት፣ ለማከማቸት፣ ለመቁላት፣ ለመቁላትና ለመፍጨት፣ ለማሸግ እና ለማጓጓዝ የሚያስችል ብቃት ያለው መሆኑን የሚያረጋግጥ አግባብ ባለው የመንግስት አካል የተሰጠ ህጋዊ ሰነድ ነው፤

፴፭ "ቡና የማሸግ ሥራ" ማለት ቡና ከአንድ ቦታ ወደ ሌላ ቦታ ለማጓጓዝ በባለስልጣኑ ወይም በክልል አካል በተፈቀደ የቴክኒክ አሰራር የተዘጋጀ ቡናን ከብክነትና ጥራት መጓደል ለመጠበቅ ተስማሚነቱ ተረጋግጦ በባለሥልጣኑ በተፈቀደ ማሸጊያ ቁሳቁስ የማሸግ አሠራር ነው፤

፴፮/ "የቡና ገለባ" ማለት ቀይ እሸት ቡና በሚፈለፈል፣ ጀንፈል ወይም የታጠበ ቡና ከነገለፈቱ በመቀሸርና በማበጠር ከዋናው የቡና ምርት የሚለይ እርጥብ ወይም ደረቅ ሽፋን ሆኖ እስከ አንድ በመቶ ንፁህ ቡና ሊኖርበት የሚችል የቡና ተረፈ ምርት ነው፤

፴፯/ "የወጪ ቡና ሽያጭ ውል" ማለት ቡናን በጥሬው፣ ቆልቶ ወይም ቆልቶና ፈጭቶ አዘጋጅቶ የሚልክ ቡና ላኪ በተለያዩ መዳረሻ ሀገራት ቡና ሲሸጥ በዋጋ፣ በመጠን፣ በምርት ዓይነትና ጥራት ደረጃ፣ የመላኪያ ጊዜ፣ የክፍያ ሁኔታ

public or private enterprise established in the coffee producing areas and issued with certificate of competence and business license by the Authority to inspect quality and to grade supply coffee;

26/ "coffee quality inspection and certification center" means a center established to inspect level of quality and issues certificates of quality and county of origin for raw, roast or roast and grind export coffee;

27/ "coffee transaction centers" include first level coffee transaction centers and the Ethiopian Commodity Exchange;

28/ "coffee trade" means acts including buying coffee from producers or produce, processing and supplying to the Ethiopia Commodity Exchange, exporting row or roasted or roasted and grinded coffee, distributing, retailing with license from the appropriate government organ;

29/ "domestic consumption coffee wholesaler" means a person who, upon being licensed to trade coffee by the appropriate government organ and fulfilling the requirements set, and upon purchases domestic consumption coffee from the Ethiopian Commodity Exchange, distribute only for coffee retailers in the designated market;

30/ "coffee retailer" means a person who has obtained certificate of competence and business license from appropriate government organ for retail trade in domestic consumption coffee and purchases this coffee only from wholesaler engaged in domestic consumption coffee

ዝርዝር ከውጭ ሀገር ቡና ገዢ ደንበኛው ጋር በሚፈራረም በኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ ዕውቅና አግኝቶ የተመዘገበ የተፈጻሚነት ግዴታ ያለው ሰነድ ነው፤

፴፰/ "የቅይጥ ቡና ዝግጅት" ማለት ባለስልጣኑ በሚፈቀደው የቴክኒክ አሠራር መሠረት የተለያየ ባህሪ ያላቸው ቡናዎች በማቀላቀል በተለየ ራሱን የቻለ መለያ ስም የሚዘጋጅ በጥሬ ወይም እሴት የተጨመረበት ቡና ነው፤

፴፱/ "አገልግሎት ሰጪ" ማለት በባለሥልጣኑ ወይም አግባብ ባለው የክልል አካል የአገልግሎት ሰጪነት የብቃት ማረጋገጫ የንግድ ፈቃድ ወስዶ በቡና ማጠብ፣ ሚልፈል፣ ማበጠር፣ ወጪ ንግድ ቡና ማዘጋጀት፣ መቁላት፣ መፍጨት፣ ማከማቸት ወይም ማጓጓዝ አገልግሎት የሚሰጥ ሰው ነው፤

፵/ "አሳሳች ድርጊት" ማለት የቡና ዓይነት፣ ዋጋ፣ መጠን፣ የጥራት ደረጃ፣ ዝግጅት፣ ማከማቸት ወይም ማጓጓዝ በተመለከተ የገበያ ተሳታፊዎችንና መንግሥትን አሳሳች የሆነ ማንኛውም ድርጊት ነው፤

፵፩/ "ፐሎምፕ" ማለት ቡናን በጆንያ ወይም በብትን ሆኖ በኮንቴነር ወይም በጭነት መኪና ወይም በባቡር ተሞልቶ ከተጫነ በኋላ ወደ ምርት ገበያ ወይም ወደ ወጪ ምርት ማዘጋጃ ኢንዱስትሪ ወይም እሴት ወደ ሚጨምሩ ኢንዱስትሪዎች ወይም ወደ ጅምላ ነጋዴ ወይም ወደ ወደብ ወይም ከማዘጋጃ ኢንዱስትሪ ወደ ሌላ ማዘጋጃ ኢንዱስትሪ ለመላክ በሽቦ ታስሮ በብረት መጨፍለቅ ወይም ማሸግ ነው፤

፵፪/ "ባለሥልጣን" ማለት በሚኒስትሮች ምክር ቤት በደንብ የተቋቋመ የኢትዮጵያ ቡናና ሻይ ባለስልጣን ነው፤

፵፫/ "አስፈጻሚ አካል" ማለት ሚኒስቴሩ፣ ባለሥልጣኑ፣ የኢትዮጵያ ምርት ገበያ ወይም በዚህ አዋጅ የቡና ግብይትና ጥራት ቁጥጥር ሥራን አስመልክቶ የሚወጣውን ደንብና መመሪያ እንዲያስፈጽም በህግ ሥልጣን የተሰጠው የፌደራልና ክልል አካል ነው፤

፵፬/ ''አግባብ ያለው የክልል አካል'' ማለት የክልል የቡናና ሻይ ባለሥልጣን ወይም ተመሳሳይ ሥልጣንና ተግባር የተሰጠው አካል ነው፤

፵፭/ "ክልል" ማለት በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገ መንግሥት አንቀጽ ፵፯ የተመለከተው

business;

31/ "export coffee roaster" means a person who has obtained certificate of competence and business license from appropriate government organ to purchase export coffee from the Ethiopia Commodity Exchange, or from other transaction options or collects from his own farm and roasts or roasts and grinds coffee for export market by maintaining appropriate standard;

32/ "domestic coffee roaster" means a person who has obtained a certificate of competence and business license from appropriate regional government organ to purchase domestic consumption coffee from the Ethiopia Commodity Exchange, and roasts or roasts and grinds coffee for sale in the domestic market;

33/ "Out growers scheme" means a legal relationship between certified coffee producer investors in coffee development and borderline and nearby coffee farmers based on mutual interest through extension services and technological support for improvement of productivity and production quality and transaction;

34/ "competence certificate" means a legal document issued by the appropriate government organ that certifies the ability of a person to carry out coffee transaction, process, store, roast, roast and grind, pack and transport;

35/ "coffee packaging" means a packaging of processed coffee with appropriate materials to transport from one place to another in allowed technical procedures by the Authority or regional body to protect wastages and quality defects of

ማንኛውም ክልል ሲሆን የአዲስ አበባ እና የድሬዳዋ ከተማ አስተዳደሮችን ይጨምራል፤

፵፮/"ሚስቴር" ወይም "ሚስትር" ማለት እንደቅደም ተከተሉ የእርሻና ተፈጥሮ ሀብት ሚስቴር ወይም ሚስትር ነው፤

፵፯/ "ሰው" ማለት ማንኛውም የተፈጥሮ ሰው ወይም በህግ የሰውነት መብት የተሰጠው አካል ነው፤

፵፰/በዚህ አዋጅ በወንድ ጾታ የተገለጸው ድንጋጌ የሴትንም ፆታ ይጨምራል፡፡

## ፫. የተፈጻሚነት ወሰን

ይህ አዋጅ በኢትዮጵያ የቡና ግብይትና ጥራት ቁጥጥር ላይ በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ በሚሰተፍ ማንኛውም ሰው ላይ ተፈጻሚ ይሆናል፡፡

## ክፍል ሁለት
## የቡና ጥራትና ግብይት አሰራር

## ፬. ቡና ጥራት ቁጥጥር አሠራር

፩/ በክልል ሥልጣን የተሰጠው የቡና ጥራት ተቆጣጣሪ አካል፡ -

ሀ) በመጀመሪያ ደረጃ ወይም በሌሎች በተፈቀዱ የግብይት አማራጭ ቦታዎች የሚካሄደውን ቀይ እሸት እና የጀንፈል ቡና ግብይት በጥራት ላይ ተመስርቶ መፈጸሙን ክትትልና ቁጥጥር ያካሂዳል፤

ለ) ቡና ማዘጋጃ ኢንዱስትሪ አስፈላጊውን ብቃት ያለው ዝግጅት ማድረጉን፣ በተፈቀደ የቴክኒክ አሠራር ቡና ስለማዘጋጀቱ፣ ስለቡና አያያዝና አከማቻቸት ክትትልና ቁጥጥር ያደርጋል፤

ሐ) ቡና ከተመረተበት አካባቢ አዋጁን ለማስፈጸም በሚወጣው በደንብ ወይም መመሪያ በሚወሰነው መሠረት አስፈላጊውን ቅድመ ሽኝት መረጃ አረጋግጦ በፕሎምፕ አሽጎ በማሸኛ ሠነድ አስደግፎ ወደ ህጋዊ መዳረሻው ይሸኛል፤ መድረሱንም ክትትልና ቁጥጥር ያደርጋል፡፡

፪/ የቡና ጥራት ምርመራና ደረጃ ምደባ ማዕከል የደረሰ የአቅርቦት ቡና በአግባቡ ታሽጎ መድረሱን በማረጋገጥና ወካይ ናሙና በመውሰድ አስፈላጊውን የጥራትና የጣዕም

coffee;

36/ "coffee husk" means a wet or dry cover find out of pulped red cherry coffee, coffee with pulp or washed coffee with parchment, hulled, cleaned, sorted coffee by product which may contain about 1% of clean coffee;

37/ "export coffee contract" means an enforceable agreement signed between coffee exporter and foreign coffee buyer to sale row, roast, roast or grind coffee to different destinations and by describing price, amount, type and quality standard level, exporting date or shipment date and conditions of payment and recognized and registered by the National Bank of Ethiopia has obligation of implementation the same;

38/ "mixed coffee processing" means a process of mixing different types of coffee in accordance with its own trade name and the appropriate technical procedure of the Authority;

39/ "service provider" means a person who, upon being licensed to provide service by the Authority or appropriate regional organ and fulfilling the requirements set, engaged in coffee wash, pulp, clean and sort, export coffee processing roast, grind, store or transport;

40/ "manipulation" means any act that results or is likely to result in confusion or deception of market participants or the Government as to the price, quantity, quality level, process type or storing or transporting of coffee;

41/"seal" means an act of sealing, closing or packing of coffee with a device or substance into a sack or a container or a

ምርመራ በማድረግ ደረጃ ይመድባል::

፫/ ባለሥልጣኑ የጥራት ደረጃ የተሰጠውንና አስፈላጊው መረጃ የተሟላለትን ቡና የግብይት ሂደቱ ሲጠናቀቅ ወደ የወጪ ቡና ማዘጋጃ ኢንዱስትሪዎች በፐሎምፐ አሽጎ ይሸኛል፣ መድረሱንም ክትትልና ቁጥጥር ያደርጋል፡፡

፬/ ባለሥልጣኑ የወጪ ገበያ ቡና ከአገር ከመውጣቱ በፊት በተመረተበት ሥነ-ምህዳር አካባቢ ባህሪና ስያሜ ወይም በባለስልጣኑ በተፈቀደ የቅይጥ ዝግጅት ምጣኔ መሠረት ማዘጋጀቱን ያረጋግጣል::

፭/ ባለሥልጣኑ የጥራት ደረጃው በቡና ጥራት ምርመራና ሰርተፊኬሽን ማዕከል የተሰጠውን የጥራት ደረጃና የምርት ሀገር የምስክር ወረቀት በማስጠት በፐሎምፐ አሽጎ ወደ ወደብ ይሸኛል፤ መድረሱንም ይከታተላል፣ ይቆጣጠራል፡፡

፮/ በኢትዮጵያ ምርት ገበያ ወይም በባለስልጣኑ የተፈቀደለት ሌላ የምርመራ ማዕከል ለሀገር ውስጥ ፍጆታ የሚውል ቡና የተቀመጠውን ማስፈርት ማሟላቱን በማረጋገጥ የደረጃ ምደባና የምስክር ወረቀት በማስጠት ወደ ተጠቃሚ አከባቢዎች ይሸኛል፤ መድረሱንም ይከታተላል ይቆጣጠራል፡፡

፯/ ባለሥልጣኑ ለሀገር ውስጥና ለወጪ ገበያ በተዘጋጀ ቡና በተሰጠ የጥራት፣ ምርመራና የደረጃ ምደባ ላይ በሚቀርቡ ቅሬታዎች ላይ ወሳኔ ይሰጣል፡፡

## ፫. <u>የቡና ግብይት አሠራር</u>

የቡና ግብይት አሠራር በሚከተለው ሜለክ ይከናወናል:-

፩/ ቀይ እሸት ወይም የጀንፈል ቡና ግብይት አነስተኛ ይዞታ ባላቸው አርሶ አደሮች ወይም አልሚ ባለሀብቶች ወይም በአቅራቢዎች ወይም በህብረት ሥራ ማህበራት ወይም በልማትና ግብይት ትስስር በፈጠሩ አልሚ ባለሃብቶች ወይም እሴት በሚጨምሩ ኢንዱስትሪዎች መካከል፤

፪/ የአቅርቦት ቡና ለውጭ ገበያ ለማዘጋጀት የሚውል ከሆነ በአቅራቢና በላኪ መካከል ወይም በአቅራቢ እና በኤክስፖርት ቡና ቆዪ መካከል፤

፫/ የአቅርቦት ቡና ሆኖ የውጭ ገበያ ደረጃ ካላሟላ በአቅራቢና በጅምላ ነጋዴ ወይም በሀገር ውስጥ ቡና ቆዪ መካከል፤

vehicle or a train to transport to commodity exchange or export coffee processing industries or value added industries or wholesaler or port or from processing industries to other processing industries;

42/ "Authority" means the Ethiopian Coffee and Tea Authority established by the Council of Ministers Regulation;

43/"executing organ" means the Ministry, the Authority or Ethiopia commodity exchange or a regional or federal executing organ authorized by law to execute a regulation and directive issued for the proper execution of coffee marketing and coffee quality in accordance with this Proclamation;

44/ "relevant regional organ" means regional Coffee and Tea Authority or other organ designated with the same power and function;

45/ "regional state" means any State referred to in Article 47 of the Constitution of the Federal Democratic Republic of Ethiopia and includes the Addis Ababa and Dire Dawa city administrations;

46/ "Ministry" or "Minister" means the Ministry or Minister of Agriculture and Rural Natural Resources, respectively;

47/ "person" means any natural or juridical person;

48/ any expression in the masculine gender includes the feminine.

## 3. <u>Scope of Application</u>

፬/ ከወጪ ገበያ ምርት ዝግጅት የሚወጣ ተረፈ ምርት ቡና ከሆነ በላኪ እና በሀገር ውስጥ ፍጆታ ቡና ጅምላ ነጋዴ ወይም በሃገር ውስጥ ቡና ቆዪ መካከል በግብይት ማዕከላት፤

፭/ በኢትዮጵያ ምርት ገበያ የሚፈጸም የአቅርቦት ቡና ግብይት በምርት ገበያ ወይም በባለስልጣኑ በተፈቀደላቸው የግል የቡና ጥራት ምርመራና ደረጃ ምደባ ማዕከላት በተሰጠው የጥራት ደረጃና ባለቤትነትን ገላጭ የሆነ በተሟላ መረጃ ማስረት፤

፮/ በዚህ አንቀጽ ንኡስ አንቀጽ (፪)፤ (፫) እና (፬) የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ በሌሎች የግብይት አማራጮች የሚፈጸም የአቅርቦት ቡና ግብይት ይህን አዋጅ ለማስፈጸም በሚወጣው ደንብ በዝርዝር በሚወሰነዉ መሠረት በባለስልጣኑ እየተመዘገበ ይከናወናል፤

፯/ በኢትዮጵያ ምርት ገበያ ሆነ በሌሎች የግብይት አማራጮች የተሸጠ የአቅርቦት ቡና ለወጪ ገበያ ዝግጅት ከዝርዝር መረጃው ጋር ወደ ቡና ማዘጋጃ ኢንዱስትሪ ይሸኛል፤

፰/ የአቅርቦት ቡና ደረጃ ከወጣለት ቀን ጀምሮ በኢትዮጵያ ምርት ገበያው አሰራር በሚፈቀደው የጊዜ ገደብ በመኪና ላይ ወይም ባለቤትነትን ገላጭ በሆነ መንገድ ተከማችቶ ይሸጣል፤

፱/ በመኪና ላይ በጊዜ ገደቡ ያልተሸጠ የአቅርቦት ቡና በኢትዮጵያ ምርት ገበያ ወይም የመጋዘን አገልግሎት ለማስጠት በተፈቀደላቸው ድርጅቶች መጋዘን ብቻ ባለቤትነትን ገላጭ በሆነ አግባብ በማቆየት ለገበያ ይቀርባል፤

፲/ የሀገር ውስጥ ፍጆታ ቡና በኢትዮጵያ ምርት ገበያ ብቻ ለጅምላ ነጋዴዎች ወይም ለሀገር ውስጥ ቡና ቆዪዎች በጨረታ ይሸጣል፤

፲፩/ቡና አልሚ ባለሃብቶች አነስተኛ ይዞታ ካላቸው ቡና አምራች አርሶ አደሮች ጋር ይህን አዋጅ ለማስፈጸም በሚወጣው ደንብ መሠረት የልማትና ግብይት ትስስር በመፍጠር የእሸት ወይም የጀንፈል ቡና ግብይት ማካሄድ ነው፤

፲፪/ቡና ላኪዎች በኢትዮጵያ ምርት ገበያ ወይም በሌሎች

This Proclamation shall apply to any person who directly or indirectly involves in coffee marketing and quality control.

## SECTION TWO
## COFFEE QUALITY CONTROL AND MARKETING PROCESS

### 4. Coffee Quality Control Process

1/ The legally designated regional quality control organ shall:

a) Inspect transaction of red cherry coffee and coffee with pulp in first level or other transactions options, based on the set standard quality.

b) Inspect and supervise competence of coffee processing industries and supervise the handling, storing and processing are carried out in accordance with appropriate technical procedure.

c) Inspect the locality of production and pre-release document and send with release document as closed with seal to the legal destination and follow up its end.

2/ The coffee quality inspection and grading center shall verify that the coffee arrived is properly sealed and grade through an appropriate examination based on a representative sample.

3/ The Authority shall send the sealed graded coffee to the export coffee processing industries after the necessary document is completed and shall supervise its process.

የግብይት አማራጮች የገዙትን ወይም በማሳቸውና በትስስር ያመረቱትን እንዲሁም ቆልተው ወይም ቆልተውና ፈጭተው ያዘጋጁትን ቡና ለውጭ ሀገር ቡና ገዢዎች በማሻጥ የሽያጭ ውል ሰነድ በብሔራዊ ባንክ ያስመዘግባሉ፤ ለባለሥልጣኑ ያሳውቃሉ፤

፲፫/የወጪ ንግድ ደረጃ ያለው እሴት የተጨመረበት ቡና ተፈጥሯዊ ጣዕምና ባህሪውን ለማስተዋወቅ ሲባል በደንብ በሚፈቀደው ቦታና ጊዜ መሠረት በሀገር ውስጥ በውጭ ምንዛሪ ብቻ ለሽያጭ ሊቀርበ ይችላል፡፡

፲፬/የቡና እሴት የሚጨምሩ ኢንዱስትሪዎች ይህንን አዋጅ ተከትሎ በሚወጣ ደንብ መሠረት ከውጭ ሀገር ጥሬ ቡና ማስገባት ይችላሉ፡፡

**፮. <u>የቡና ገለባ ግብይት</u>**

፩/ በባለሥልጣኑ ወይም አግባብ ባለው የክልል አካል በሚሰጠው የብቃት ማረጋገጫ ማሰረት ማንኛውም ቡና አምራች ወይም አዘጋጅ ወይም ከህጋዊ አካል ቡናን የገዛ ሰው በዝግጅት ሂደት የሚወጣውን የቡና ገለባ አዘጋጅቶ ለሀገር ውስጥ ወይም ለወጪ ገበያ ሊያቀርብ ይችላል፡፡

፪/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) የተገለጸው እንደተጠበቀ ሆኖ አግባብ ካለው የመንግስት አካል ፈቃድ የወሰደ ሰው የቡና ገለባን በጥሬ ዕቃነት ተጠቅሞ የተፈጥሮ ማዳበሪያ ወይም ወደ ሌሎች ምርቶች ቀይሮ ጥቅም ላይ ማዋል ይቻላል፡፡

## <u>ክፍል ሶስት</u>

## <u>የግብይት ተሳታፊ ግዴታዎች</u>

**፯. <u>በቡና ግብይት ሥራ የተሰማራ ሰው ግዴታዎች</u>**

ማንኛውንም በቡና ግብይት የተሠማራ ሰው:-

፩/የቀይ እሸትና ጀንፈል ቡና ግብይት በተፈቀዱ የቡና ማዘጋጃ ኢንዱስትሪዎች ወይም አግባብ ባለው የክልል አካል በተፈቀደ የመገበያያ ስፍራ ብቻ የማካሄድ፤

፪/የአቅርቦት ቡና ግብይት በኢትዮጵያ ምርት ገበያ ወጪ በተፈቀዱ ሌሎች የግብይት አማራጮች የሚፈጸም ከሆነ የቡና ዓይነት፣ ማጠን፣ ጥራት ደረጃ፣ ዋጋና ጊዜ በባለስልጣኑ

4/ The Authority shall inspect that the coffee is prepared in accordance with the standards set for mixed coffee processing containing the characteristics and name of agro-ecology of its production area before it is exported.

5/ The Authority shall send to the port for consignment, the sealed and certified coffee graded by coffee quality inspection and leveling center and shall follow up its end.

6/ other inspection center allowed by the Ethiopian Commodity Exchange or the Authority shall seal and send domestic consumption coffee to consumer regions upon verification of leveling and issuance of a certificate and shall follow up to its final destination.

7/ The Authority shall decide on complaints presented in domestic and export coffee quality inspection and leveling.

**5. <u>Coffee Transaction Process</u>**

Coffee transaction shall take place as follows:

1/ red cherry coffee or coffee with pulp between small scale farmers or commercial growers, coffee suppliers or co-operative associations or out growers or value adding industries;

2/ if supply coffee is intended for export, between a coffee supplier and a coffee exporter or a coffee supplier and an export coffee roaster;

3/ if supply coffee does not fit for export level, between a coffee supplier and a wholesaler or between a domestic coffee

በማስመዝገብ የሚፈጸም፤

፫/ የአቅርቦት ቡና በሀገር ወስጥ ለግብይት ከመቅረቡ በፊት በልዩ ሁኔታ በባለስልጣኑ የተፈቀደለት ካልሆነ በስተቀር በቡና ጥራት ምርመራና ደረጃ ምደባ ማዕከል አስመርምሮ የምስክር ወረቀት የማግኘት፤

፬/ የአቅርቦት ወይም የወጪ ቡና ከመጫኑ በፊት አሽከርካሪወና ተሽከርካሪወን የብቃት ማስፈርት አሟልቶ ማስማራቱን የማረጋገጥ፤

፭/ በባለሥልጣኑ ወይም አግባብ ባለው የክልል አካል የተሰጠ የብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት የማቅረብ፤

፮/ ለግብይት ካዘጋጀው ቡና ለጥራት ምርመራ አገልግሎት የሚውል ናሙና እንዲሰጥ ሲጠየቅ **ወካይ ናሙና የመስጠት ወይም የማቅረብ፤**

፯/ ማንኛውንም ቀይ እሸት ወይም ጀንፈል ቡና ከባለሥልጣኑ ወይም አግባብ ካለው የክልል አካል ከተፈቀደ የማበያያ ሥፍራ ወደ ሚፈልፈያ ወይም መቀሸሪያ ኢንዱስትሪ ከማጓጓዙ በፊት ህጋዊ ሰነድ የመያዝ፤

፰/ ማንኛውንም የአቅርቦት ወይም የወጪ ገበያ ቡና ከማጓጓዙ በፊት በፕሉምፐ ማሸግና በተቆጣጣሪው የተሰጠውን ሰነድ የመያዝ፤

፱/ ዕለታዊ የቡና ግዢና ሽያጭ መጠን፣ ደረጃ፣ ዋጋና ሌሎች ዝርዝር መረጃዎች መዝግቦ የመያዝና ለባለሥልጣኑ ወይም ለሚመለከተው ተቆጣጣሪ የማሳወቅ፣ ወይም በአካል ለመነብኘት ወይም ክምችት ለመቁጠር ሲፈለግ የመተባበር፤

፲/ የአገሪቱን የቡና ጥራት ማስፈርት የማክበርና እና የቡናችንን መልካም ሥም ከሚያጎድፉ ማንኛውም ድርጊቶች የመቆጠብ፤

፲፩/ይህን አዋጅ ለማስፈፀም የሚወጡ ደንቦች፣ መመሪያዎች እና የአሠራር ሥርዓቶች የሚፈፀምና የማስፈጸም ግዴታዎች አሉበት፡ ፡

፰. <u>የቡና አምራች ግዴታዎች</u>

ማንኛውም የቡና አምራች፡ –

፩/ ከአርሶ አደር በስተቀር፣ ከሚመለከተው የመንግስት አካል የተሰጠ የጸና የብቃት ማረጋገጫ እና ንግድ ፈቃድ የመያዝ፤

roaster;

4/ if it is coffee by product, between an exporter and a domestic consumption wholesaler or a domestic coffee roaster and a wholesaler or between a domestic coffee roasters in transaction centers;

5/ supply coffee transaction in the Ethiopia Commodity Exchange shall be carried out on the basis of the grade and point issued by private coffee quality inspection and grading centers and based upon complete ownership descriptions;

6/ without prejudice to the provisions of sub-article (2), (3) and (4) of this Article, supply coffee transaction in other alternative transactions shall be conducted with registration, in Authority in accordance with a regulation to be issued for the execution of this proclamation;

7/ coffee sold in the Ethiopia Commodity Exchange or other transaction options shall be sent to the processing industries for export preparation with the details of relevant information;

8/ supply coffee starting from the date of grading shall be sold on vehicle in accordance with permitted procedures of the Ethiopian Commodity Exchange or store and with description of ownership;

9/ coffee not sold on a vehicle with in the limited duration, may be stored only in the Ethiopia Commodity Exchange or in allowed enterprises that provide warehousing services with description of ownership;

10/ coffee for domestic consumption shall be traded for wholesalers or domestic coffee roasters only in the Ethiopia Commodity Exchange by auction;

፲፩/ በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፫ ንኡስ አንቀጽ (፩) የተጠቀሰው እንደተጠበቀ ሆኖ ያመረተውን የአቅርቦት ቡና በቀጥታ ወደ ውጭ ለመላክ ሲፈልግ ወደ ኤክስፖርት ማዘጋጃ ኢንዱስትሪ አሳሽጎ የማሸኘትና የወጪ ምርት ዝግጅት ሲያጠናቅቅ ጥራት ምርመራና ሰርተፊኬሽን ማዕከል አቅርቦ ደረጃ የማረጋገጥና የማሸኘት፤

፲፪/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) የተጠቀሰው እንደተጠበቀ ሆኖ በኢትዮጵያ ምርት ገበያ ወይም በሌሎች የግብይት አማራጮች በሀገር ውስጥ የሚገበያይ ከሆነ ለቡና ጥራት ምርመራና ደረጃ ምደባ ማዕከል አቅርቦ ደረጃ የማስጠት፤

፲፫/ ቡና አልሚ ባለሀብት አነስተኛ ይዞታ ካላቸው ቡና አምራች አርሶ አደሮች በልማትና ግብይት ትስስር ቡና ለመግዛት የኤክስቴንሽንና የቴክኖሎጂ አቅርቦት ድጋፍ የማድረግ፣ ከወቅቱ የተሻለ ዋጋ የመክፈል ወይም በውል ስምምነታቸው መሠረት ከሽያጭ በኋላ ትርፍ የማከፋፈል፤

፲፬/ ተረፈ ምርት ቡና በቡና ጥራት ምርመራና ደረጃ ምደባ ማዕከል አስመርምሮ ሲፈቀድ ብቻ በኢትዮጵያ ምርት ገበያ የመሸጥ፤

፲፭/ ያመረተውን ወይም በልማትና ግብይት ትስስር የገዛውን ቡና በኢትዮጵያ ምርት ገበያ ወይም በሌላ ህጋዊ የግብይት አማራጭ የምርት ዘመኑ ሳያልፍ የመሸጥ ወይም ወደ ውጭ አዘጋጅቶ የመላክ ግዴታዎች አሉበት፡፡

## ፮. <u>የቡና አቅራቢ ግዴታዎች</u>

ማንኛውንም ቡና አቅራቢ፡ –

፩/ ቀይ እሸት ወይም ጀንፈል ቡና በተፈቀደለት አካባቢ ብቻ የመግዛት፣ የማዘጋጀት፣ የማጓጓዝ፣ የበቀለበትን አካባቢ ቡና ባህሪና ስያሜ የመጠበቅ፣ ከሌላ ሥነ-ምህደር ዓይነት ቡና ጋር ሳይቀይጥ ወይም ከማንኛውም ሌሎች ባዕድ ነገሮች ሳይደባለቅ የማቅረብ፣

፪/ የገዛውን ቀይ እሸት ቡናን በደንቡ በባለሥልጣኑ በተፈቀደ የቴክኒክ አሠራርና ጊዜ መሠረት የታጠበ ቡና ከነገለፈቱ፣ በከፊል የታጠበ ቡና ወይም ተፈጥሯዊ ቡና የማዘጋጀት፣

፫/ የሚያዘጋጀውን የአቅርቦት ቡና በኢትዮጵያ ምርት ገበያ ወይም በሌላ ህጋዊ የግብይት አማራጭ የምርት ዘመኑ

11/ cherry coffee or coffee with pulp transaction shall be made with commercial coffee growers and small scale farmers through coffee out growers contractual agreement in accordance with the regulation issued for the execution of this Proclamation;

12/ coffee exporters shall register to National Bank of Ethiopia and notify to the Authority, the export coffee contracts of coffee purchased from the Ethiopia commodity Exchange or in other alternative transaction or produced in their own farm and coffee roasted, roasted and grinded sold in foreign market;

13/ graded and value added export coffee only can be sold in foreign exchange in domestic market to promote the natural taste and origin in accordance with the place and time stated in the regulation.

14/ industries engaged in value addition may import raw coffee from abroad in accordance with a regulation to be issued following this Proclamation.

## 6. <u>Coffee Husk Transaction</u>

1/ In accordance with the certificate of competence provided by the appropriate regional body or the Authority, any coffee producer or processor or a person who legally buys coffee, may deliver the processed coffee parchment to domestic or foreign market.

2/ Without prejudice to the sub-article (1) of this Article, a person who has a license from relevant government organ may use coffee husk for making natural fertilizer or changing it to other products.

ሳያልፍ የማሸጥ ወይም ወደ ውጭ አዘጋጅቶ የመላክ፣

፬/ ለቡና ጥራት ምርመራና ደረጃ ምደባ ማዕከላት የሚያቀርበው ወይም በቀጥታ ለላኪ የሚሸጠውን ወይም በራሱ አዘጋጅቶ ቀጥታ ወደ ውጭ የሚልከውን የአቅርቦት ቡና ጥራቱን የጠበቀና የእርጥበቱ ማጠን ወይም ይዘት ይህንን አዋጅ ተከትሎ በሚወጣው ደንቡ በሚወሰነው መሠረት መሆኑን የማረጋገጥ፣

፭/ በቡና ጥራት ምርመራና ደረጃ ምደባ ማዕከል ተመርምሮ ለውጭ ገበያ ብቁ የሆነ የአቅርቦት ቡና በኢትዮጵያ ምርት ገበያ የማሸጥ ወይም

፮/ አስቀድሞ በሌላ አማራጭ የግብይት ትስስር የተሸጠ ከሆነ ለገዥው የማስረከብ ወይም

፯/ የተሻለ ዋጋ ለማጠበቅ ያሰበ እንደሆነ በቡና ግብይት ባልተሰማሩ ህጋዊ የማከማቻ አገልግሎት የማስጠት ፍቃድ ባላቸው ድርጅቶች የማከማቸት፣

፰/ የምርት ዘመኑ የቡና ግብይት ከመጀመሩ በፊት አስፈላጊውን ቅድመ ዝግጅት ስለማጠናቀቁ ከሚመለከተው የክልል አካል የብቃት ማረጋገጫ የመያዝ ግዴታዎች አሉበት፡፡

## ፰. የቡና ላኪ ግዴታዎች

ማንኛውም ቡና ላኪ፡ –

፩/ ከሚመለከተው የመንግስት አካል የተሰጠ የፀና የብቃት ማረጋገጫ እና ንግድ ፈቃድ የመያዝ፤

፪/ ወደ ውጪ የሚልከውን ቡና የአገሪቱን የጥራት ደረጃ ማስፈርት ጠብቆ የማዘጋጀት፣

፫/ በባለስልጣኑ በልዩ ፍቃድ ካስመዘገበው የቅይጥ ቡና ዝግጅት ውጭ ቡናው በተመረተበት አካባቢ ባህሪና ስያሜ ጠብቆ ለውጭ ገበያ የማቅረብ፣

፬/ የውጪ ቡና ሽያጭ ውል ስምምነት ከፈፀመ ፳፬ ሰዓት ባልበለጠ ጊዜ ውስጥ በኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ የማስመዝገብ እንዲሁም ለባለስልጣኑ በሦስት የስራ ቀናት ውስጥ የማሳወቅ፣

፭/ በማናቸውም የግብይት አማራጮች የገዛውን ወይም ያመረተውን ወይም ህብረት ስራ ማህበር ከሆነ የቡና ማሳ ካላቸው አባላቱ የሰበሰበውን ቡና ምንም ሳያባክንና

## SECTION THREE
## OBLIGATIONS OF TRANSACTING ACTORS

### 7. Obligations of Person Involved in Coffee Transaction

Any person involved in coffee transaction shall:

1/ conduct a transaction of red cherry coffee and coffee with pulp only in transaction centers or coffee processing industries which are allowed by the appropriate regional organ;

2/ if supply coffee transaction takes place in other alternative transaction options outside Ethiopia Commodity Exchange, the coffee type, quality standard, quantity, price and date shall be registered and carried out in the Authority

3/ unless it is allowed in special directive by the Authority, acquire a certificate from the coffee quality inspection and grading center before submitting supply coffee to domestic coffee transaction;

4/ ensure, before loading supply or export coffee for transportation, that a vehicle and its driver comply with competence standard;

5/ submit competence certificate issued by the Authority or the appropriate regional organ;

6/ submit a representative sample from the coffee prepared for transaction when so requested for quality inspection purposes;

7/ get a legal letter of release before transporting any red cherry coffee and coffee with pulp from the transaction center permitted by the Authority or appropriate regional organ to pulp or hull coffee industries;

የጥራት ደረጃው ሳይጓደል በምርት ዘሙ ለውጭ ሀገር ገበያ የማሸጥ፣

፮/ ለውጪ ገበያ በማዘጋጀት ሂደት የሚወጣ ተረፈ ምርት ቡና ወደ ኢትዮጵያ ምርት ገበያ በማቅረብ የማሸጥ፣

፯/ አሳማኝ ምክንያት መኖሩ በባለሥልጣኑ ተረጋግጦ በኢትዮጵያ ብሐራዊ ባንክ መራዘሙ እንደተጠበቀ ሆኖ ከገዢዎች ጋር የገባውን ውል በውሉ ጊዜ ውስጥ የመፈጸም፣

፰/ በቡና ጥራት ምርመራና ደረጃ ምደባ ማዕከል ተመርምሮ ለውጪ ገበያ ብቁ የሆነ ቡና በልዩ ምክንያት በባለሥልጣኑ ካልተፈቀደ በስተቀር በኢትዮጵያ ምርት ገበያ ወይም በሌላ የግብይት አማራጭ በአገር ውስጥ ለግብይት ያለማቅረብ ግዴታዎች አሉበት፡ ፡

## ፲፩ .<u>የሀገር ውስጥ ፍጆታ ቡና ጅምላ ነጋዴ ግዴታዎች</u>

ማንኛውም የሀገር ውስጥ ፍጆታ ቡና ጅምላ ነጋዴ፡ –

፩/ ከሚመለከተው የመንግስት አካል የተሰጠ የፀና የብቃት ማረጋገጫ እና ንግድ ፈቃድ የመያዝ፤

፪/ የሀገር ውስጥ ፍጆታ የሚሆን ቡና ከኢትዮጵያ ምርት ገበያ ብቻ የመግዛት፣

፫/ የውጪ ገበያ ቡና አለመግዛት ወይም አለማጓጓዝ ወይም አለማሸጥ፣

፬/ የሀገር ውስጥ ፍጆታ ቡናን በጅምላ ለማከፋፈል ንግድ ፈቃድ በወሰደበት ክልል ወይም ዞን ወይም ከተማ ብቻ የማሸጥ፣

፭/ የሀገር ውስጥ ፍጆታ ቡናን ከኢትዮጵያ ምርት ገበያ ወደ ተጠቃሚ ክልል ወይም ዞን ወይም ከተማ ሲያጓጉዝ በባለስልጣኑ የሽኝት ሠራተኞች በፕሎምፕ ማሳሸግ፣ የማሸኛ ሠነድ የመያዝና ሲጠየቅ የማሳየት፣ እንደታሸገ መድረሱንም ከሚመለከተው አካል ማረጋገጫ የመውሰድና ለባለስልጣኑ የማቅረብ፣

፮/ የዘሙ የቡና ግብይት ከመጀመሩ በፊት አስፈላጊውን ቅድመ ዝግጅት ስለማጠናቀቁ ከሚመለከታቸው የመንግሥት አካላት የብቃት ማረጋገጫ የመያዝ ግዴታዎች አሉበት፡ ፡

## ፲፪ .<u>የሀገር ውስጥ ፍጆታ ቡና ቸርቻሪ ነጋዴ ግዴታዎች</u>

8/ have appropriate executive body seal and issue a letter of release when transporting any supply or export coffee;

9/ maintain a register of the daily coffee exchange quantity, grade, price and list of purchase and disclose such register to the Authority or relevant inspection and cooperate when physical presence for site visit or inventorying is required;

10/ refrain from all acts that may damage the good name of the country's coffee and respect the quality standards of the country;

11/ comply with and cause to implement all regulations, directives and procedures enacted by the appropriate body for the proper execution of this Proclamation.

## 8. <u>Obligation of Coffee Producers</u>

Any coffee Producer shall:

1/ except farmer, hold valid competence certificate and trade license from appropriate government organ,

2/ without prejudice sub-article (1) Article 5 of this Proclamation, have the right to directly export coffee from his own farm, only after submitting the same to the coffee quality inspection and grading center for grading before and after processing for export;

